*ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ*

*Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity*

Efdpu@aol.com www.Finote.org

*ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 13 ሜትር ባንድ*

*Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on n25 meter band*

**መስከረም 12 ቀን 2006 ዓ.ም.**

# ዜና ዘገባ

## የህወሀት ነባር ታጋይና ባለስልጣናት ስርዓቱን ጥለው እየኮበለሉ መሆኑ ተጋለጠ

በወያኔ ቡድን ውስጥ የተጀመረው ፍትጊያ እና ንትርክ ከቀን ወደ ቀን እያየለና እየሰፋ በመምጣቱ ነባር የበረሀ ታጋይ የነበሩና በአሁኑ ሰዓት የሀገሪቱ ቁልፍ ስልጣን ላይ የተቀመጡ ሁሉ ስርዓቱን እየከዱ ወደ ውጭ ሀገር እየኮበለሉ መሆኑ ታወቀ፡፡

የህወሀት አንጋፋ ታጋይ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው አርከበ እቁባይም በህወሀት ውስጥ በተፈጠረው ክፍፍል እና ንትርክ የተነሳ አውሎ ንፋስ እንደሚንጠው ውሀ ከዚያና ከዚህ እየተላተመ በመሆኑ ለስራ በሚል ከሀገር መውጣቱን የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስታውቀዋል፡፡

የህወሀት ነባር ታጋዩና ስርዓቱ ስልጣን ላይ ከወጣ በሁዋላ የተለያዩ ቁልፍ ኃላፊነቶች ላይ ተቀምጦ የነበረው አርከበ እቁባይ በደረሰበት መገለል ምክንያት ይከፋና ይተክዝ እንደነበር የጠቆሙት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ባለፈው ሳምንት ለስራ በሚል ከታናሽ ወንድሙና ከመላ ቤተሰቦቹ ጋር ወደ አሜሪካ መውጣቱን ምንጮቹ ገልጸዋል፡፡

ወያኔ የአራት ኪሎ ቤተ መንግስትን ከተቆጣጠረበት ግዜ ጀምሮ ከኤፈርት ስራ አስኪያጅነት እስከ ትግራይ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንትነት ....ከአዲስ አበባ ከንቲባነት እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር አማካሪነት በስልጣን ማማ ላይ ሲምዘገዘግ የነበረው አርከበ እቁባይ በህወሀት ውስጥ የተፈጠረው ውጥረት እና ጡዘት አልመች እንዳለው ሲነገር የቆየ ቢሆንም አሁን በድንገት ቤተሰቦቹንና የወንድሙን ቤተሰቦች ይዞ ከሀገር መውጣቱን ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል፡፡

በሕወሀት ክፍፍል ወቅት በተፈጠረው ሽኩቻ ለእስር በተዳረገው ስዬ አብርሀ ላይ በሀሰት እንዲመሰክር በመለስ ዜናዊ ተገድዶ እንደነበር ያስታወሱት ምንጮቹ ለዚህ ውለታው ከትግራይ ክልል ምክትል ፕሬዝዳንትነት ወደ አዲስ አበባ ከንቲባነት እንዲሸጋገር ተደርጎ እንዲሰራ መደረጉን ያስታወሱት ምንጮቹ በአዲስ አበባ ሕዝቡን በማደራጀት እና አነስተኛና ጥቃቅን የሚባሉትን ለወያኔ እንዲያድሩ በማድረግ የተሳካ ስራ ስርቶ የነበረ ቢሆንም በመለስ ዜናዊ በኩል ግን አልዋጥለት ስላለው ከከንቲባነት አንስቶ የስራና ከተማ ልማት ምክትል ሚኒስትር ሆኖ በአንድ ጠባብ ቢሮ እንዲወሸቅ ያደረገው መሆኑን ምንጮቹ አስታውሰዋል፡፡

በዚህ ብቻ ሳይበቃ መተካካት በሚል ከሕወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነት እንዲወገድ አድርጎ ለይስሙላ ሹመት በሚመስል መልኩ በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ አማካሪ ሆኖ እንዲቀመጥ ከተደረገበት ግዜ ጀምሮ ይከፋና

ያዝን እንደነበር ምንጮቹ ጠቁመው በአሁኑ ሰዓትም በህወሀት ውስጥ በተፈጠረው ልዩነት አቁዋም ለመያዝ ተቸግሮ ግራ ተጋብቶ ባለበት ወቅት ድንገት ቤተሰቦቹን ይዞ ወደ አሜሪካ መጉዋዙን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የወያኔ ንብረት የሆነው ከ50 ድርጅቶች በላይ የሚያስተዳድረው ኤፈርት ከፍተኛ ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ የነበረው የአርከበ እቁባይ ታናሽ ወንድም የሆነው ጌታቸው እቁባይም ቤተሰቦቹን ይዞ ከወንድሙ ጋር አብሮ የተጉዋዘ መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ ገልጸዋል፡፡

በህወሀት ውስጥ የነበረው ክፍፍል መለስ ከሞተ በሁዋላ እየጎላና እየሰፋ በመምጣቱ የተነሳ በተለያዩ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰሩትን አባሎቻቸውንና አመራሮችን ለየራሳቸው ቡድን ደጋፊ ለማድረግ በሚደረገው ሽኩቻ አቁዋም ባለመያዙ እንደ ወንድሙ ግራ ተጋብቶ ባለበት ወቅት ከስራ እንዲሰናበት ተደርጎ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ወደ ሀገረ አሜሪካ መሄዱን ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

አርከበ እቁባይ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ሲሰራ የሴቶች ፎረምን ሰብስቦ ባነጋገረበት ወቅት እጅግ ከፍተኛ ድጋፍ እና ሙገሳ ሲደረግለት አዜብ መስፍን በመበሳጨት ይሄንን ሁሉ እያደረገ ያለው መለስ የሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸሙ ብቻ እንጂ በራሱ አይምሮ አፍልቆ የሰራው አይደለም በማለት በወቅቱ አስደንጋጭ መልዕክት ካስተላለፈች በሁዋላ መለስም በበበኩሉ በኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ አርከበ ውጤት ያላመጣ..... የተሰጠውን ትዕዛዝ በአግባቡ መፈጸም ያልቻለ..... ከተማዋን በቀለም ቅብ ብቻ ያስዋበ ነው በማለት ከፍተኛ አመራሮቹ ጭምር እንዲስቁበት ካደረገበት ግዜ ጀምሮ በመለስ ጥርስ ውስጥ ገብቶ እንደነበርና አሁንም ብዙ ደስተኛ እንዳልነበር የጠቆሙት ምንጮቹ በቅርቡ ቤተሰቦቹን ለስራ ብሎ ይዞ መውጣቱ ምናልባትም ግለሰቡ በዚያው ለመቅረት አስቦ የወሰደው እርምጃ ሳይሆን እንደማይቀር የጠቆመ ምልክት ነው ተብሎዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ውጥረት ውስጥ ባለበት ባሁኑ ወቅት ከአባልነቱ እና ከባለስልጣንነቱ እራሱን አግልሎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመምህርነት ሲያገለግል የቆየው ሌላው የህወሀቱ ሰው ሙሉጌታ በርሔም ሰሞኑን ወደ አሜሪካ ማቅናቱ ተጠቆመ፡፡

ሙሉጌታ በርሄ የተባለው የሕግ መምህር ከወያኔ ተገንጥሎ ከወጣ በሁዋላ አስደንጋጭ ተቃውሞ እና ትችት ሲሰነዝርበት እንደነበር የጠቆሙት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በተለይ የሙስሊሙ ሕብረተሰብ ያነሳውን የሙብት ጥያቄ ደግፎ በተለያዩ በውጭ ሀገር ከሚሰራጩ የመገናኛ ብዙሀኖች ጋር ቃለ ምልልስ ሲያደርግ የነበረ መሆኑን ምንጮቹ ገልጸዋል፡፡

በወያኔ ቡድን ውስጥ የተፈጠረው ችግር እየሰፋና እያደገ የመጣ ሲሆን በተለይ የህወሀቶቹ ክፍፍል እና ንትርክ አስጊ ደረጃ ላይ በመድረሱ የቀድሞዎቹ የህወሀት ባለስልጣናት ስርዓቱን ከመታደግ ይልቅ እራሳቸውን ለማዳን እየተራወጡ መሆኑ ወያኔ የመጨረሻው መጀመሪያ ላይ መድረሱን ያመላከተ ነው ተብሎዋል፡፡

## በትግራይ ሕዝቡ እየታሰረ እና እየተገደለ መሆኑ ተጋለጠ፤

የህወሀት ባለስልጣናት በቡድን ተከፍለው ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ ባሉበት በዚህ ግዜ ክልሉን በአስተዳደራዊ ስራ ሊመራ የሚችል ኃይል ባለመኖሩ የትግራይ ህዝብ ለከፋ ችግር መዳረጉን ሕዝቡ በይፋ ገለጸ፡፡

የሕወሀት ካድሬዎች መለስ ከሞተ በሁዋላ ለመጀመሪያ ግዜ በየወረዳው እየተዘዋወሩ የሕዝቡን ስሜት ለማጤን ባደረጉት ሙከራ እንደተረዱት ከሆነ ህወሀት ደከሞ እራሱን መምራት ያልቻለ በመሆኑ ክልሉ ለከፋ አስተዳደራዊ በደሎች እየተዳረገ ነው ሲሉ ሕዝቡ መናገሩ ታውቆዋል፡፡

ዛሬ በትግራይ ክልል የወረዳና የቀበሌ አመራሮች የሚቆጣጠራቸው ጠፍቶ በህዝቡ ላይ እንደልባቸው ከመጨፈራቸውም ባሻገር ያለ አንዳች ጥፋት ከደርግ ግዜ በባሰ ሁኔታ ሕዝቡን ያስራሉ .....ያሰቃያሉ....ይገድላሉ ሲሉ የክልሉ ነዋሪዎች በምሬት ሲናገሩ እንደነበር ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

ለፖለቲካ መጠቀሚያ ሲሉ የህውሄን ከተማን በደርግ የጦር አውሮፕላን ሲያስደበድቡና ሕዝቡን ሲያስጨርሱ የነበረ ቢሆንም ዛሬም ያች ከተማ እንደወደመች እና አንዳችም የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴ ያልተደረገባት ከመሆኑም በተጨማሪ ሕዝቡ የልማት ጥያቄ በማንሳቱ ሴት ወንድ.... ወጣት ሽማግሌ ሳይሉ እያሰሩ እየገደሉዋቸው እንደሆነና ከደርግ ጅምላ ጭፍጨፋ ያልተናነሰ በደል እየተፈጸመባቸው መሆኑን ነዋሪዎቹ እየገለጹ ይገኛሉ፡፡

የመለስን ራዕይ እናስፈጽማለን እያሉ እየዳከሩ የሚገኙትን የወያኔን የወረዳና የቀበሌ መሪዎች የትግራይ ሕዝብ በቁጣ አሳፍሮ የመለሳቸው ሲሆን በተለይ የሽሬ እና የሁመራ አውራጃ ነዋሪዎች መለስ በሕይወት እያለም አንዳችም የረባ መሰረተ ልማቶች እንዲከናወኑ ሳያደርግ አሁን ከሞተ በሁዋላ በሙት መንፈስ ራዕዩን እናስፈጽማለን ማለታችሁ አስገራሚ ብቻ ሳይሆን ከሞተው ግለሰብ ጋር ሀሳባችሁ አብሮ የተቀበረ በመሆኑ በእኛ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም ብሎ አሳፍሮ እንደመለሳቸው ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡

ወትሮም ሀገራዊ አጀንዳ ያልነበረው.....የሀገሪቱን ሕዝቦች ለአገዛዙ እንዲመቸው በጎጥ እና በመንደር እየከፋፈለ ሲያምሰን እንዳልነበር...የትግራይን ሕዝብ ከተቀረው የሀገሪቱ ሕዝቦች ለያይቶ ዳግም እንዳንገናኝ እንዳላደረገ ዛሬ በመለስ ራዕይ የተጀመሩትን እናስፈጽማለን መባሉ የማይሆንና የማይዋጥልን ነው ሲሉም መናገራቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወገኖቹ እንዳይገናኝ እና ጨርሶ እንዲለያይ ያላሰለሰ ጥረት ስታደርጉ ነበር ያለው ሕዝቡ ለሰራችሁት ስህተት እና ጥፋት በይፋ ይቅርታ ካልጠየቃችሁ አሁንም ሆነ ወደፊት ከናንተ ጋር አብረን አንኑዋዝም በማለት ሕዝቡ ለ‹ድሬዎቹ አስደንጋጭ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ታውቆዋል፡፡

በሕዝቡ ሀሳብ ተስማምተው የተመለሱ የወረዳ ካድሬዎች በቀጥታ ለክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣናት የህዝቡን ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ሕዝቡን ያሳመጻችሁ እናንተ ናችሁ በሚል ከስልጣናቸው መባረራቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

መቀሌ የሚገኘው በአባይ ወልዱ የሚመራው አንዱ የወያኔ ክንፍ ካድሬዎቹን ወደ ተለያዩ ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ልኮ የህዝቡን የልብ ትርታ አድምጠው እንዲመለሱ የላካቸው ቢሆንም ይዘው በመጡት መልስ በመደናገጥ ከአዲስ አበባው ቡድን ጋር ወግናችሁዋል በሚል ከስልጣናቸው ያባረታቸው መሆኑን ከመቀሌ የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

ከፍተኞቹ የህወሀት ባለስልጣናት እርስ በርስ መተማመን ተስኖዋቸው አንዱ አንዱን በጥርጣሬ እያየ ባለበት በዚህ ግዜም ባለፈው ሳምንት በመቀሌ በተደረገው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎች ስብሰባ ላይ ንትርክ እና ጭቅጭቅ የነበረ ሲሆን በቅርቡም የተለያዩ ሹም ሽሮች ይደረጋሉ ተብሎ እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

በአሁኑ ሰዓት የመቀሌው በአባይ ወልዱ የሚመራው ቡድን የትግራይ ክልል መንግስታዊ መዋቅሩን ተጠቅሞ የአዲስ አበባውን ቡድን ከህዝቡ ለማራቅ ሙከራ እያደረገ ሲሆን በአንጻሩ በደብረጽዮን የሚመራው ይመራል እየተባለ የሚነገርለት የአዲስ አበባው ቡድን ደግሞ በሙስና ሰበብ እያሰረና ከስልጣናቸው እያነሳ በመገኘቱ በህወሀት ውስጥ የተፈጠረው ሽኩቻ እየሰፋና እየገዘፈ መምጣቱ እየተነገረ ይገኛል፡፡

በቅርቡም በመቀሌ ከተማ በተደረገው የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ የእነ አባይ ወልዱ ቡድን በእነ ደብረጽዮን ላይ የበላይነቱን ለመያዝ ሲል አዲስ አደረጀጃጀት እና አዳዲስ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባሎችን ለማምጣት በስውር ሰፊ ስራ እየሰራ እንደሚገኝም ተጠቁሞዋል፡፡

የእነ ደብረጽዮን ቡድን ደግሞ ለሀገር ሳይሆን ለስልጣን ....ለሕዝብ ሳይሆን ለግለሰቦች በማሰብ እና ያኛውን ለማዳከም የሙስና ምንጠራ እያደረጉ ሲሆን የህወሀት ቁልፍ ሰው ከተባለለት የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣኑ ገብረዋህድ ቀጥሎ የደህንነት ምክትል ኃላፊ የሆነውን ግለሰብ ጭምር ዘብጥያ በማውረዳቸው ትንቅንቁ እንደቀጠለ፤ አመላች ሆኖዋል፡፡

መለስ በሕይወት እያለ የሚስቱን ገመና ለመሸፈን ሲል በሙስና እስከ አንገታቸው ድረስ የተዘፈቁ ቁጥራቸው የበዙ የወያኔ ባለስልጣኖች መኖራቸውን እያወቀ ስልጣኔን ካልተጋፉ ምን ቸገረኝ በሚል ስሜት የነበረ ቢሆንም እሱ ከሞተ በሁዋላና አሁን በህወሀት መሀከል በተፈጠረ ትርምስ ምክንያት በተጀመረው የሙስና ምንጣሮ ከፍተኛ ፈላጭ ቆራጭ የሆኑ ግለሰቦች ዘብጥያ የወረዱ ሲሆን ከነዚህ ግለሰቦች ጋር በሽርክና ስትሰራ የነበረችውና በቢሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት ያሸሸችው አዜብ መስፍን ጉዳይም ለግዜው በሚል በእንጥልጥል የቆየ ይሁን እንጂ የደብረጽዮን ቡድን ከተጠናከረ ሴትዮዋም ዘብጥያ መውረድዋ አይቀሬ እንደሆነ በስፋት እየተነገረ ይገኛል፡፡

ለዚህም ማሳያ ከኤፈርት ዋና ስራ አስኪያጅነት ተነስታ ከሌሎችም ወሳኝ ቦታዎች ተገድባ የመለስ ፋውንዴሽን ላይ ብቻ ተመድባ እንድትሰራ መደረጉ ወደፊት የነደብረጽዮን አቁዋም እየጠነከረ ከመጣ ያለ ማወላወል ከጉዋደኞችዋ ጋር እስር ቤት ልትቀላቀል ትችላለች ተብሎዋል፡፡

## <u>የወያኔ ባለስልጣናት በክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ እጅግ አደገኛ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ከፈቱ</u>

የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት የውስጥ ችግሮቻቸውን መፍታት ተስኖዋቸው እርስ በርስ የጎሪጥ እየተያዩ ባሉበትና ሙስለሙ ሕብረተሰብ ያነሳውን የፍትሕ ጥያቄ ለመመለስም ሆነ ውጥረቱን ለማርገብ ባልቻሉበት በዚህ ግዜ በክርስቲያኑ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ቅስቀሳ መጀመራቸው ታወቀ፡፡

በስብሀት ነጋ አይዞህ ባይነት በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተክለማርያም ጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢነት በአፍሪካ ሕብረት መሰብሰቢያ አዳራሽ በተደረገው ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ውስጥ ወንጀል እንደሚፈጸምና አክራሪዎችም እንዳሉ በመግለፅ በይፋ መናገሩ ታውቆዋል፡፡

መያዣ መጨበጫው የጠፋባቸው የወያኔ ባለስልጣናት የሙስሊሙን ሕዝብ ጥያቄ ከሽብርተኝነት ጋር በማያያዝ የጥላቻ ዘመቻ ቢከፍቱም አልሳካ ሲላቸው በቅርቡ ደግሞ በክርስትና እምነት ተከታዮች ላይ እጅግ አስፈሪ የሆነ ቅስቀሳ መጀመራቸው ታውቆዋል፡፡

ስብሀት ነጋ ሰሞኑን በስብሰባው ላይ እና በተለያዩ የወያኔ ሚዲያዎች ላይ እንዳንጸባረቀው ከሆነ የክርስትና እምነት ተከታዮችም ጀርባቸው ሊጠና እና ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል ብሎ በመናገሩ በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ቁጣን መቀስቀሱ ታውቆዋል፡፡

እንደፈለገውና ያሻውን እየተናገረ የሚዘላብደው ይሄው የወያኔ ባለስልጣን ስብሀት ነጋ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ብቻ ሳይሆን በኦርቶዶክስም ውስጥ አክራሪ እና ጽንፈኞች ስላሉ ጉዳዩን በጥልቀት ተከታትለን ልንመረምረው ይገባል በማለት በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ላይ ጣቱን መቀሰሩም ታውቆዋል፡፡

የውስጥ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ያልቻሉት የወያኔ ቡድን ከፍተኛ ባለስልጣናት የራሳቸውን የውስጥ ችግር ለመሸፋፈን ሲሉ ሰላማዊ ጥያቄ ያቀረበውን የሙስሊሙን ህብረተሰብ ሽብርተኛ የሚል ተቀፅላ ሰጥተው አንገቱን እንዲደፋ ለማድረግ ቢሞክሩም አልሳካ ሲላቸው አሁን ደግሞ ፊታቸውን ወደ ክርስትና እምነት ተከታዮች ማዞራቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆኑም በተጨማሪ የሀገርና የህዝብ ከፋፋይ ሴራ ነው ሲሉ የእምነቱ ተከታይ ምሁራኖች በንዴት ይገልጻሉ፡፡

የወያኔ ከተማ አፈራሽ ባለስልጣኑ የደኢህዴኑ ሽፈራው ተክለማርያም አቀረበ በተባለው ጥናታዊ ጽሁፉ ላይ በሀገራችን በሁሉም ሀይማኖቶች በተለይ በኦርቶዶክስ እምነት ሽፋን...በእስልምና እምነት ሽፋን....በፕሮቴስታንት እምነት ሽፋን አክራሪነትንና ፅንፈኝነት አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ እንቅስቃሴ አራማጆች የተከማቹበት በመሆኑን አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል በማለት የወያኔን አቁዋም መግለጹን ተከትሎ ሕዝቡ በሰላም አንገቱን ደፍቶ በመኖሩ ፍርሀት ስላደረባቸው ብቻ ሊያምሱት ከላይ እታች ማለታቸው አስገራሚ ነው ተብሎዋል፡፡

የህዝበ ክርስቲያኑ ዝምታ ያስደነገጠው የወያኔ ቡድን ከውስጥ ችግሮቹ ጋር ተዳምሮ አላስቀምጥ ስላለው ብቻ በተለያዩ ምክንያቶች ሕዝቡን ስብሰባ እየጠራ የክርስትና እምነት ተከታይ አክራሪዎች ስለተፈጠሩ ልትጠነቀቁ ይገባል እያለ ምንም ባልተፈጠረበት እና ሰላማዊ በሆነችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውዥንብር መፍጠሩ አስገራሚና አሳፋሪ እጅግ አደገኛ በመርዝ የተለወሰ ፕሮፓጋንዳ መሆኑን ሕዝቡ ሊረዳ ይገባል ሲሉም የእምነቱ ተከታይ ምሁራኖች ተናግረዋል፡፡

ተስፋ የቆረጠው እድሜ ጠገቡ ስብሀት ነጋ በበኩሉ በአሁኑ ሰዓት የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን የፖለቲካ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚፈልጉ ኃይሎች እየተንቀሳቀሱባት በመሆኑ መንግስት አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል ሲል ማሳሰቢያ መስጠቱም ተደምጦዋል፡፡

ስብሀት ነጋና የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ሽፈራው ተክለማርያም በሰጡት ማስጠንቀቂያ ላይ የማሕበረ ቅዱሳን አባላት ጽንፈኛና አክራሪዎች በመሆናቸው ክትትል ሊደረግባቸው ይገባልም ብለዋል፡፡

የወያኔ አቀንቃኝ የነበሩት አባ ጳውሎስ ከሞቱ በሁዋላና አቡነ ማትያስ ከተተኩ ወዲህ በቤተክህነት ውስጥ ከላይ እስከ ታች ድረስ በብሔር ተመድበው ያለ እውቀታቸው የተቀመጡ እንዲነሱ በመደረጉ እንዲሁም በአዲስ አበባ በሚገኙ ርዕሰ አድባራት ውስጥ ቤተክርስቲያንን ሲያምሱ.... ሕዝበ ክርስቲያኑን ሲጫወቱበት የነበሩ ከወያኔ ጋር ቅርብ ግንኙነት ያላቸው ካድሬ ካሕናት በመመንጠራቸው ስጋት የገባቸው የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት የተባረሩትን ለመመለስ በማሰብ ሕዝበ ክርስቲያኑን አክራሪ እና ሽብርተኛ እያሉ ተለጣፊ ስም እየሰጡ እያስፈራሩ ይገኛሉ፡፡

አዲሱ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ ገና በተሾሙ ጥቂት ቀናት ውስጥ ሲኖዶሱን ሰብስበው በቤተክህነትም ሆነ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያለ እውቀትና ችሎታቸው ተመድበው የተቀመጡ ግለሰቦች እንዲነሱና ሌሎች እውቀት ያላቸው በቦታው እንዲቀመጡ በማድረጋቸው የተደናገጡት የወያኔ አቀንቃኝ እና ተላላኪ ካህናቶች ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር በመሆን የተጀመረውን ምንጠራ ለማስቆም አሽባሪና ጽንፈኛ እያሉ ቢያስፈራሩም አሁንም ድልድሉና ምንጠራው እንደቀጠለ ከቤተክህነት የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል፡፡